# ቆዳውን ገልብጦ የለበሰ ሰውነት

**ሰውን ነው ሰው ማለት ሰውነቱን አይቶ**
**ሰብዕናው ከሸሸው ሰውነቱን ከድቶ**
**ካለበሰ አካሉን ቆዳውን ገልብጦ**
**እንዴት ሰው ይሆናል ሰብዕናውን ሽጦ?**

**አብርሃም በየነ**

ዕምነትና ክህደት የመኖርንና የመሞትን ያክል ቁርኝት እንዳላቸው ህይዎት አስተምሮናል። ያመነ ይድናል እንደሚለው ቅዱስ መጽሐፍ የካደም አዳምን ይሆንና ዕርግመቱን ይኖሩታል። ዕምነት ማተብ ነው። ማተብም ቃል። ቃል ደግሞ ከሽክም ይከብዳል። ያመኑት ከሚከዳ የወለዱት ይሙት እንደሚሉት አበው። ዛሬ ግን ማተብን በጥሶ ማተብ አልባ መሆን የአራዳነት ባርኔጣ ሲያስጭን ተስተውሉዋል። ቃል አባይነት ደግሞ በዛሬው የአብሽሎ ዘመን የሰለጠነ ፖለቲካ ተብሉዋል። እነ አዜብ ጌታቸውም እንደ ካባ ደርበውት ሊያጌጡበት መሽቀርቀር ጀምረዋል።

ስለ ክህደት ሲወሳ የናዚ ወንጀለኞችን ለመዳኘት በኑረምበርግ በተሰየመው ፍርድ ቤት የፍትህ ሂደት ወቅት የተከናወነን አንድ አጭር ድራማ ያስታውሰኛል። ጁሊየስ ስትራይቸር የተባለው አይሁድ ወገኖቹ አይሁዳውያን ከናዚ ዕይታ ተሰውረው ህይዎታችውን ለማትረፍ በተደበቁበት ስፍራ እየተከታተለ ጠቁሞ በወገኖቹ ላይ የፈፀመውን የክህደት ወንጀል አልታወቀብኝም ብሎ በአንድ የግብርና ቤት (farm house) ገላውን ሰዶ ሲዝናና አሜሪካዊው አይሁድ ሻለቃ- ሄነሪ ብሊት ጥላውን ሆኖ ሲከታተለው ከቆየ በሁዋላ ከዕለታት በአንደኛዋ ቀን ይይዘውና በጭዋታቸው መሃከል "ናዚዎች ምን ይመስሉሃል?" ብሎ ይጠይቀዋል። ጁሊየስም "እኔ አርቲስት ነኝ ስለፖለቲካ የማውቀው ነገር የለኝም" ብሎ ሲመልስለት ሻለቃው መልሶ በፌዝ መልክ "ግን ጁሊየስ ስትራይቸርን ትመስላለህ" ሲለው ጁሊየስ እንደ ክረምት አሞሌ መወርዛት ጀመረ።

ጌታቸውም እኔ መሆኔ አይታወቅብኝም መስሎት አዜብ ጌታቸውን ሆኖ "የኢሕ አፓ-ዴ"ን ፈጠራ የራሱ ፈጠራ ላለማስመሰል የጁሊየስ ስትራይቸርን ባህሪይ ተላብሱዋል።

አዜብና ጌታችው ደግሞ በዛሬዋ ኢትዮጵያ የዘመናችን ጁሊየሶች መሆናቸውን ማንም የሚስተው ነገር ነው በየ አልጠራጠርም። ወ/ሮ አዜብ (ቀዳማይ ዕመቤት ልበላትና) ወልቃይቴ ወገኖቹዋን ለናዚ ወያኔዎች አሳልፋ የሰጠች ከሃዲ ነች።

ጌታቸው በጋሻውም ለዘመናት አብረውት ሲታገሉ የወደቁትን ሰማዕታትና ለዘመናት የታገለበትን መርህ ክዶ ቆዳውን ገልብጦ የለበሰ የክህደት አባውራ ሁኑዋል።

እናም አዜብና ጌታቸው በክህደት ባህሪያቸው ሰኔንና ሰኞን ሆነው በመገጣጠም "ኢሕአፓዎች ዛፍ ያጣ ጉሬዛ አትሁኑ" ሲሉ ለተነኮሱት አተካሮ መልስ ለመስጠት ብዕር አነሳሁ።

("ኢሕአፓዎች ዛፍ ያጣ ጉሬዛ የመሆን ስጋት ከፈጠረው አሉታዊ እንቅስቃሴ ራሱን ሊገታ የገባዋል። በነገራችን ላይ ዛፍ ያጣ ጉሬዛ የሚለው ተረት ስርዎ መነሻን አስመልክተው አንድ አባት ስለ ጉሬዛ ባህሪ ያወጉኝን እኔም ላውጋችሁና የዛሬውን ፅሁፌን ልቋጭ።"

በፀሎተኝነቱ የሚታወቀው ጉሬዛ ልቡም ትራራ ነው አሉ። ዛፍ ላይ ሆኖ በአናቱ ሰማይ ላይ አውሮፕላን ሲያልፍ ዛፉን እየነውቀነቀ ብስጭቱን ይገልፃል። ያለኔ ፈቃድ እንዴት በግዛቴ ያልፋል ነው .......አሉ ብስጭቱ። እናም በልቡ ያረፈበት ዛፍም ሆነ ያካባቢ ወ አዛዥ እሱ ነው። አደን ሲያባረው እንኩዋ ለራሱ የሚያዝበት ዛፍ ካላገኘ በስተቀር ከሌሎች ጋር አንድ ዛፍ ላ ትጥግቶ ለማምለጥ ስለማይፈቅድ የብቻው የሆነ ዛፍ እስኪያገኝ መቁነጥነጥና መረበሽ ነው፣ ሲሉ ከረዥም ግዜ በፊት አንድ አባት አውግተውኛል። ዛፍ ያጣ ጉሬዛ .." የሚለው ተረትም መውደቂያ መከለያ መጠጊያ ማጣት ልሚፈጥረው ጭንቀት እንደ ምሳሌ የሚጠቀሰው ለዚህ ነው።

እናም የኢሕ አፓ ጭንቀት የጉሬዛው ዓይነት መጠጊያ አጣን ካልሆነ በስተቀር ለሌላው ኢትዮጵያዊ ዜጋ የማይታየው ለንሱ ብቻ የሚታይ "ኢትዮጵያ አንደንት ላይ ያንዣበበ የተደቀነ ስጋት የለም። ሊኖርም አይችልም። ስጋት ካለ አብረን እናየዋለን ለገዜው ግን የለም። ከዋናው ጠላት ከወያኔ በስትቀር ማለቴ ነው።

ለዛሬው ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ...... በማለት በዚሁ አሰናበታለሁ") ይላል አዜብ ጌታቸው።

የሁዋላውን ወደፊት የፊቱንም ወደ ሁዋላ አደረግኸው አትበሉኝና በጨው ልጀምር። ኢሕአፓ የነ ጌታቸው የጎሳ ፖለቲካ ማጣፈጫ ጨው ከሚሆን ድንጊያ ተብሎ በሽክላ ድስታቸው ላይ ቢወረወር ይመርጣል።

ጌታቸው ለስሙ መምህር ነው። ያውም የኮሌጅ። የሆነ ሆኖ ግን ኤቲክስ፤ሞራሊቲና አመክኖ(ሎጂክ) ከጌታቸው ባህሪይ የሚቀዱ አለመሆናቸውን ሳስበው ለተማሪዎቹ አዘንኩላቸው። ጌታቸው አይደለም ሌላውን አፉን የፈታበትን አማርኛ እንኩዋ በቅጡ መጠቀም የማይችል ሰው ነው። ይህን ስላችሁ ግን አማርኛውን ለምን አታስተምረውም እንዳትሉኝ። እርሱን ሰለ ቃላት አሰካክና ስለ ዐረፍተ ነገር ብሎም ስዋሰው ከማስተማር ደንጊያ መውቀርን እመርጣለሁ። ቢያንስ ድንጋዩ ተወቅሮ ሲሆን ጤፍ ካልሆነም ገብስ ሊፈጭ ይችላል።

ጌታቸው ግን ተወቅሮም ትምሮም ሰው የሚሆን ሰው አይደለም። ምንም ቢሆን ምን ዶ/ር ዜሮ ያው ዶ/ር ዜሮ ነው። ዜሮነቱን የሚጠራጠር ካለ ስለጉሬዛው የዘባረቀውን ቅባጥርሴ ተመልክቶ ትዝብቱን መውሰድ ይችላል። የሆነው ሁሉ ሆኖ ግን የጉሬዛዎቹ ሃቅ እንዲህ ነው፦

ጉሬዛዎች በባህታዊ ይመሰላሉ። አንድም በአኑዋኑዋራቸው- በቤተክርስቲያን ዛፎች ላይ ስለሚሰፍሩ፣ አለያም በአመጋገባቸው- ቅጠላቅጠል እና ፍራፍሬ ስለሚመገቡ፤ ወይም በሁለቱ ጣምራ ባህሪያት በባህታዊ ይመሰላሉ። በቆላማው የኢትዮጵያ ክፍል በሚገኙት አብያተ-ክርስቲናት በየደብሮቹ ዛፎች ሰፍረው ሲኖሩ የሚታወቁት ጉሬዛዎች ቀን ቀን ከዛፎቹ ላይ ሳይወርዱ ሲውሉ የሚመለከታቸው ሰው ዕውነትም ባህታዊያን ናቸው ይላቸዋል።

ቀን ቅጠል ሲቆርጡ ስለማይታዩ በዓሎችንም የሚያከብሩ ይመስላሉ። ሃቁ ግን ጉሬዛዎች እንደ ሌሊት ውፎችና ጉጉቶች (nocturnal) ስለሆኑ ቀን ቀን የማየት ችግር አለባቸው። እናም ከዛፋቸው ወርደው አይንቀሳቀሱም። ስለሆነም ጉሬዛዎች የሌሊት ወፎችና ጉጉቶች ምግባቸውን የሚፈልጉት በቀን ሳይሆን በሌሊት ነው።

ዛፍ ያጣ ጉሬዛ የሚለው ተረትም የተተረተባቸው ለምግብ ፍለጋ ጉሬዛዎቹ ከመኖሪያ ስፈራቸው እርቀው ሲሄዱና ሲመለሱ ሲነጋባቸው በፀሀዩ ብርሃን የሚጭበረበረው ዐይናቸው የዕውር ድንብስ ጉዞ ሲያስጉዛቸው በሚያሳዩት የመተራመስ (መደነባበር) ባህሪይ ነው ተረቱ የተተረተባቸው እንጂ ጌታቸው ፈጠሮ አዛውንቱ ነገሩኝ እንዳለው አውሮፕላን በላያቸው ላይ ስለ ጮኸ በንዴት ለምን ግዛቴ ተደፈረ ከሚል ድንፋታ የመነጨ አልነበረም።

ለነገሩ ጌታቸው ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ ያምራል ሲሉ ሰምቶ ነው እርሱም "ሲሉ ሰምታ ዶሮ ሞተች ከጭስ ገብታ" እንዲሉ ዶሮዋን የሆነው።

ዳሩ ጌታቸው በጉሬዛው ተረት አስመስሎ በተጎላደፈ አማርኛ ኢሕአፓን ሊነካ የፈለገባቸውን ነጥቦች ተረድቸለታለሁ። እነርሱም፤-

- ከኦነግ ጋር የተጀመረው ውይይት ያለኔ ፈቃድ እንዴት ይሆናል? ("ያለኔ ፈቃድ እንዴት በግዛቴ ያልፋል ነው….አሉ ብስጭቱ")
- ከሌሎች ደርጅቶች ጋር አብሮ ለመስራት ያለመቻል ችግር አለበት ("አደን ሲያባረው አንድ ዛፍ ላይ ተጠግቶ ለማምለጥ ስለማይፈቅድ….. መቁነጥነጥና መረበሽ")

- በመሆኑም ተነጥሎ ስለቆመ መጠጊያ ከማጣት የተነሳ ጭንቀት ወርሶታል("....የሚለው ተረትም መውደቂያ፥ መከለያ፤ መጠጊያ ማጣት")

- ስለሆነም ከነዚህ ሁሉ ችግሮች ለመላቀቅ ኢሕአፓ የግንቦት7ንና የኦነግን ደጀንነት ቢሻ ይሻለዋል። አለበለዚይ ድንጋይ ነው ተብሎ ይጣላል የሚሉ እሳቤዎችን ይመስሉኛል ከስብርባሪ አማርኛው የተረዳሁለት።

የጌታቸው ክስ በዳቦ ጠብ ያለሽ ይመስለኛል። ከኦነግ ጋር የመደራደርን መብት ኢሕአፓ ሰጭና ነፋጊ ሊሆን አይችልም። ያለኔ ፈቃድ........ የሚልም ቅዠት ቃዥቶ አያውቅም። እርሱም ከኦነግ ጋር ተነጋግሮ ያውቃልና መንጋገሩን አላወገዘም። ከኦነግ ጋር መነጋገሩ በራሱ ችግር የለውም። ችግሩ ኦነግ ኢትዮጵያዊ ነኝ ሳይል እትዮጵያዊ ከሆኑ ከአንድነት ሃይሎች ጋር ህብረት እንዲፈጥር የሚታየው ሽርጉድ ነው። ኦነግ እትዮጵያዊ የመሆኑንና ያለመሆኑን ጉዳይ ራሱ መናገር ሲችል ብርሃኑ ነጋ ለኦነግ አፈቀላጤ መሆኑም ሌላው ችግር ነው። እትዮጵያዊ የመሆንና ያለመሆን መብት የኦነግ እንጂ የማንም ስለማይሆን ዜግነት ሰጭና ነፋጊ ሃይል ሊኖር አይችልም።

በኢትዮጵያዊ ዜግነት ላይ ነፋጊም ለጋሽም ሊኖር ካልቻለ ደግሞ ጥያቄው የመሆንና ያለመሆን ጥያቄ ነውና ባለቤቱም ኦነግ ነው። ስለሆነም ኦነግ ከኢትዮጵያውያን ድርጅቶች ጋር በሀገር ጉዳይ ለመወሰን እትዮጵያዊ ነኝ ማለት አለበት። ኦነግ ግን እትዮጵያዊነት እንደ አጀንዳ አሁን ሳይሆን ከወያኔ ውድቀት በሁዋላ ነው መነሳት ያለበት ባይ ነው። ኢሕአፓ ደግሞ ይህን የማዘናጊያ መላምት አይቀበለውም። ስለሆነም ኢትዮጵያዊነት መብት እንጂ ለገበያ የሚቀርብ የሸቀጥ ዕቃ ስለ አይደለ የኦነግ እትዮጵያዊ ዜጋ መሆንና አለመሆን ለድርድር አይቀብርም። እትዮጵያዊ ሆኖ ነው ከዜግነት ጥያቄ በመለስ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ለመደራደር ከአንድነት ሃይሎች ጋር ለውይይት መቀመጥ የሚችለው። ይህ ሳይሆን ግን ኦነግ የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ለመወሰን ከኢትዮጵያዊያን ጋር ስለ ኢትዮጵያ የሚያነጋግር የአጀንዳ ነጥብ የለውም።ሊኖረውም አይችልም።

የነ ብርሃኑ "ኦነግ ኢትዮጵያዊ ሁኑዋል" በሉ መዋሸትም መመንጫው ይህ የኢሕአፓ አቋዋም መሆኑ አንድና ሁለት የለውም። በርሃኑና ኩባንያው ከኦነግ ጋር መነጋገር አይችሉም ሳይሆን የኢሕአፓ ክርክር ስለ ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም የሚል አካል ወሳኝ መሆን አይቻለውም ነው። ለምን? ቢሉ  ባዕድ አካል ባገሪቱ ዜጎች ህልውና ላይ የመወሰን መብት የለውምና!!!!

ብርሃኑና ጌታቸው ኢሕአፓን የሚከሱት ድርጅቱን የህብረት አቋዋም አጥተውት አይደለም። በተለይም በህብረት ጉዳይና በአብሮነት ትግል ኢሕአፓ ቀዳማይ እንጅ ዳህራይ አየደለም። የሆነ ሆኖ ግን ምሳና ይነቅዛልን? ብለው ሲጠይቁት "እንጨቶችን ሁሉ መንቀዝ ማን አስተማራቸው?" እንዲሉ በህብረት መታገልን ከማን ተምረው ነው እነ እንቶ ፎንቶ ኢሕአፓ ህብረትና የጋራ ትግል አይፈልግም ብለው የሚከሱት?

ኢሕአፓ የህብረት ትግልን "ሀ" ብሎ የጀመረው ከገዳዮቹ ከደርጎችና መኢሶኖች ጋር ነበር። ኢድሃቅንና ህብረትን መስርቶ የታገለውን ኢሕአፓን አብሮ የመስራት ፍላጎት የለውም ብሎ መከሰሱ የደንቆሮ በትር ሆድ ይቀትር ይመስለኛል። ለህብረት ትግል ኢሕአፓ ያበረከተውን ያክል ቀርቶ ኩርማኑን ያላበረከቱትን እንቶ ፎንቶዎች ለማወደስ ሲባል ይህን ድርጅት በጋራ መታገል አይፈልግም ማለቱ የሚያረጋግጠው አንድም ጌታቸው የማስታወስ ችሎታው ጥሎት የሸሸ መሆኑን አለያም ቀዳውን ገልብጠ የለበሰ ከሃዲ እንደሆነ አጉልቶ ከማሳየት ያለፈ ክሱ ሌላ ትርጉም የለውም።

ሌላው ክስ ደግሞ ኦነግና የብርሃኑ ኩባንያ ኢሕአፓን ከወያኔ ጥቃት እንዲከላከሉለት ፈልጎ ሊያስጠጉት ባለመቻላቸው ኢሕአፓ ፍርሃት ገብቶታል የሚል ነው።

የዚህ ክስ ግድምድሞሽ ከጅብ ጥቃት ለመዳን የአህያን ውሽምነት እንደጠየቀችው እንስሳ ይሆንብኛል። የብርሃኑ ያየር ላይ ጦርና የኦነግ አይበገሬ ሠራዊት ለሌላ ተጠቂ ወገን ደጀን ሲሆን ይታያችሁ። የዚህ አተካሮ ነገረ ነገሩ የሚመስለኝ ዝሆን ከጠላት ጥቃት ለመዳን በእምባጬ ዛፍ ጫካ እራሱን እንዲሸሽግ ተገደደ ነው። ጋይንቶች እንዲህ ዓይነቱን ገጠመኝ ነው "ዛፍስ ባየሽ እምባጬ" ብለው የሚሳለቁበት።

እነ እንቶ ፎንቶ የዕምቡዋይ ካብ ህብረት ወያኔን የሱናሚ ማዕበል ሆኖ ሲጠራርገው ለኢትዮጵያ ህዝብ የምስራቹን አብሳሪ ራሱ ወያኔ እንዳይሆን ፍሩ። ያኔ በነ ጌታቸው ህብረት ያልታቀፉ ድርጅቶች ፀጉራቸውን ይነጨሉ። በፖለቲካው ቁማር ተበልተዋልና።

ፖለቲካ የሰው ጌሾ፤ብቅልና እንኩሮ ይመስለኛል። ይህንንም ቅልቅል ድፍድፍ ልትሉት ትችላላችሁ። ህዝባዝዊውም ፀረ-ህዝቡም የተቀላቀሉበት የፖለቲከኛ ውጥንቅ ነውና። ይህ ውጥንቅጥ ግን እንደ ጠላው አይጠምቁት ወይ እንደ አረቄው በፍላሎት አያወጡት አለያም እንደ ጠጁ አይጥሉት ሆኖ አምቡላም በሉት ወይ ብሪንጥ አለያም አተላ ጠፍቶት አያውቅም። ፖለቲካ እንደየዘመኑ የራሱ ዝቃጭ አለው።

ከሶቪየት ህብረት መበታተን በሁዋላ ግነት ያገኘው የብሄረተኝነት ስሜትና ጥሎት ያለፈው ትኩሳት የመገንጠል አባዜ ይመስለኛል የዘመናችን የፖለቲካ አተላ። በዚህም አተላ ባንድ ወቅት ወያኔም ኦነግም ሸዐቢያም የሰከረ በሬ ሆነው ነበር።
ሆኖም በልካቸው የተሰፋውን ጥብቆ ስካራቸው ሳይበርድ ጊዜ ሻረውና ፋሽንነቱ እየከሰመ መጣ።

ስካሩ  መብረድ ሲጀምር ጠባቡን ጥብቆ አውልቆ ዘና የሚያደርገውን ኢትዮጵያውነት ለመጎናፀፍ ፍላጎት እየዳበረ መጣ። እናም ተናንት የትግራይን ሪፓብሊክ ለመመስረት ኢሕአፓን አባይ ኢትዮጵያ ይሉ የነበሩት እነ ስዬ ገብሩና መሰሎቻቸው ወደ ህሊናቸው ለመመለስ ቆም ብለው ሁለት ጊዜ እንዲያስቡ ሁኔታው አስገደዳቸው። በዚህ  ሰዓት ነው እነ ስዬ "ያወለቁትን" የጎሳ ጥብቆ ጌታቸው አንስቶ መልበስ የጀመረው።

ጌታቸውና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳም በዚህ ሰዓት ነው እርሱ  እርሳቸው ትተውት ወደ ሄዱት ጎሰኝነት እርሳቸው ደግሞ እርሱ ወደ ተወው እትዮጵያዊነት "ሲገሰግሱ" መንገድ ላይ የተላለፉት። ስለሆነም ጌታቸው የጎሳ ጠብቆ ከኦነግ ሊመፀወት ደጅ ሲጠና ጎሰኞቹ በጎን ለኢትዮጵያዊነት ማመልከቻቸውን አስገብተው ጨርሰዋል። እኔም በነዚህ የስንኝ ቋጠሮዎች  ሃተታየን ልጨምጭምና ልዝጋ።

ራሴው ራሴን - እኔው እኔነቴን
ክብሬን አዋርጄ -ጥየው ሰውነቴን
ከሰው ጠርዝ ወርጄ - ከሰውነት ወለል
በሰው አምሳል ቆሜ - እኔነት ስቀበል
እናንተም ሰው በሉኝ - እኔም ሰው ነኝ ልበል።

............................//.........................................